# የካንሰር ኪሞቴራፒ



ሰውነትዎ በቢልዮኖች ከሚቆጠሩ ሴሎች ነው የተገነባው።እነዚህም በአጉልቶ ማሳያ መሳርያ ሲታዩ ይህን ይመስላሉ።

ጤነኛ ሴሎች ይኖራሉ፣ ያድጋሉ፣ ይሞታሉ፣ አዳዲስ ሴሎች ደግሞ ይፈጠራሉ።

የካንሰር ሴሎች ጤነኛ አይደሉም። ባልተፈለጉበት ግዜ ያድጋሉ። ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ ደግሞ መፈጠራቸውን ይቀጥላሉ።



የኪሞቴራፒ መድሃኒት፣ እነዚህን ሴሎች የሚያጠፉና መባዛታቸውን የሚገታ መድሃኒት ነው። ቢሆንም፣ ጤነኛ ሴሎችን ደግሞ ሊጎዳ ይችላል። ይህም ያልተፈለጉ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል።

ጤነኛ ሴሎች ባብዛኛውን ግዜ ከኪሞቴራፒ በኋላ ወደ ነበሩበት የጤንነት ሁኔታ ይመለሳሉ።

በኪሞቴራፒው ወቅት ምንም፣ ጥቂት ወይም ብዙ ያልተፈለጉ ውጤቶች ሊደርስቡዎ ይችላሉ።

የሚደርሱብዎ ያልተፈለጉ የውጤቶች አይነቶችና መጠን እንደ የሚሰጥዎ የኪሞቴራፒ መድሃኒት ዓይነትና መጠን ሊለያይ ይችላል።



ሊደርሱ የሚችሉ ያልተፈለጉ ውጤቶች ሊለያዩ ይችላሉ፣ ቢሆንም አብዛኛውን ግዜ የሚያጋጥሙት ይህን፡ ይመሰላሉ። ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ ድካም፣ ህመምና የጸጉር መርገፍ ።

እነዚህን ያልተፈለጉ ውጤቶችን ለማስታገስ ተብለው የተዘጋጁ የተለያዩ መድሃኒቶች አሉ።

ጤነኛ ሴሎች ባብዛኙውን ግዜ ከኪሞቴራፒ በኋላ ወደ ነበሩበት ይመለሳሉ፣ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ያልተፈለገ ውጤት ቀስ ብሎ ይጠፋል።

በኪሞቴራፒ ወቅት የረገፈ (የተመለጠ) ጸጉር፣ ተመልሶ ይበቅላል።



ለእርስዎ የሚሰጥዎ የህክምና ዓይነት፣ በካንሰሩ አይነት ነው የሚወሰነው። እንደ የሚሰጥዎ የኪሞቴራፒ መድሃኒት ዓይነት፣ የሕክምናው ዓላማና ሰውነትዎ ሕክምናዎን እንዴት እንደሚቀበል ታይቶ የሚወሰን ይሆናል። ህክምና በየቀኑ፣ በየሳምንቱ ወይም በየወሩ ሊሰጥዎ ይችል ይሆናል።

ሰውነትዎ አዳዲስ ሴሎችን ለመገንባት ዕድል እንዲያገኝ፣ በሕክምናዎች መሐል እረፍት ይሰጥዎ ይሆናል።

መድሃኒቶቹን በአፍ፣ በመርፌ፣ ወይም በአይቪ መስመር ሊሰጥዎ ይችል ይሆናል።

ሐኪምዎ ለእርስዎ የሚስማሙትን የኪሞቴራፒ መድሃኒቶችንና የሕክምና ለእርስዎ እንደሚያመች ይመርጥልዎታል። ያሆነ ጥያቄ ካልዎት፣ ሐኪምዎን ይጠይቁት።

**A project by Health Roads Media and EthnoMed**
This project has been funded in whole or in part with Federal funds from the Department of Health and Human Services, National Institutes of Health, National Library of Medicine, under Contract No. HHS-N-276-2011-0008-C with the University of Washington. Thank you to Safeway Foundation for its support to Harborview Medical Center's EthnoMed for the development of cancer-related content.